
WELLINGTON REGION
EMERGENCY MANAGEMENT

# በመሬት መናወጥ ወቅት የዕቅድ ማውጫያ መመሪያ

## ይህንን ይያዙና አሁኑኑ ዝግጁ ይሁኑ




## አሁን

### 1. በአደጋ ጊዜ መረጃዎችን ይከታተሉ (ንቁ ይሁኑ)

በአደጋ ወቅት መረጃዎችን ለማግኘት የተለያዩ መንገዶች አሉ — ሬዲዮን፣ የዜና ማህደረ መረጃን (ሚዲያን)፣ ቴሌቪዥንን፣ የWREMO (የዌሊንግተን ክልል የአደጋ ጊዜ አስተዳደር ቢሮ) እና የአካባቢው ምክር ቤት የኮሙኒኬሽን መስመሮችን እንዲሁም የአደጋ ጊዜ የሞባይል ማስጠንቀቂያዎችን ጨምሮ።

የአደጋ ጊዜ የሞባይል ማስጠንቀቂያዎች የሚላኩት በህይወት ላይ አደጋ ሲጋረጥ ወይም መላውን ወይም ከፊሉን የዌሊንግተን ክልል ሊነካ የሚችል ከፍተኛ መስተጓጎል በሚኖርበት ጊዜ ብቻ ነው።

#### የተፈጥሮ አደጋ ቅድመ ምልክቶችን ይወቁ፡-

በሱናሚ አደጋ ቀጠና ውስጥ ከሆኑ እና ረጅም ጊዜ የቆየ ወይም ጠንካራ የመሬት መንቀጥቀጥ ከተሰማዎት፣ የመሬት መንቀጥቀጡ መናወጥ ልክ እንደቆመ ወዲያውኑ ወደ ከፍተኛ ቦታ ወይም በተቻለ መጠን ወደ ውስጥ (ከባህር ርቀው) አካባቢውን ለቀው ይውጡ።

#### በአደጋ ጊዜ ጥሩ የመረጃ ምንጮች፡-

- (ሪሞ)WREMO የአደጋ ጊዜ ድህረ ገጽ ይጎብኙ
  VISIT www.WREMO.nz
- (ሪሞ)WREMO የfacebook ገፅ ላይክ ያድርጉ
  LIKE facebook.com/WREMOnz
- በአካባቢዎ የሚገኘውን ምክር ቤት ማህበራዊ ድረገጽ ይጎብኙ
- የኒው ዚላንድ እና ሌሎች የአካባቢውን የሬዲዮ ጣብያዎች ያድምጡ

# በጣም ጥሩ!

## ደህንነትዎን ለመጠበቅ የመጀመርያውን እርምጃ ወስደዋል።

የዌሊንግተን አካባቢ ለመኖር ደስ የሚል ቦታ ቢሆንም ሳይጠበቁ በሚከሰቱ ነገሮች የተሞላ ነው።

ለመሬት መንቀጥቀጥ ለከባድ ንፋስ ለጎርፍ ለመሬት መንሸራተት እንዲሁም ለከባድ ማዕበል ብዙውን ግዜ ተጋልጠን እንገኛለን።

እነኝህ አደጋዎች ተመሳሳይ ተፅዕኖ ይፈጥራሉ፣ ህብረተሰቡ ከሚወደው ጋር ለመገናኘትና  አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ለማግኘት መንቀሳቀስ ይከብዳል።

ቤተሰብዎንና ህብረተሰብዎን አስቸጋሪ በሆኑ በነዚህ ቀናት፣ከትልቅ የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋዎች በኋላ በተቻለ መጠን በደህንነት በምቾት እንዴት ማዘጋጀት እንዳለብዎት በዝርዝር ለማስረዳት ሞክረናል፣

ለአደጋ ጊዜ የማስጠንቀቂያ ጥሪ እንዲደርስዎ በመመዝገብ የመጀመሪያውን እርምጃ ወስደዋል።

ዛሬ ማታ ነገና ለሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታት ምን ማድረግ እንደሚችሉ እራስዎን በማዘጋጀት የሚቀጥለውን እርምጃ ይውሰዱ።

በእርግጥ እያንዳንዱ እርምጃ ጥረት ሊደረግለት ይገባዋል፤ ተጨማሪ ጥያቄ ካለዎት እኛን ያግኙን።

**WREMO** ቡድን (የዌሊንግተን አካባቢ የአስቸኳይ ጊዜ ተቆጣጣሪ ቢሮ)

# ተሳተፉ;

## ነፃ ስለ አደጋ ጊዜ ዝግጅት ስልጠናዎች:_

ቤተሰብዎና ህብረሰተብዎን ከከባድ የመሬት መናወጥ በፊት ወይም በመሬት መናወጥ ጊዜ እንዲሁም በኋላ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለማስረዳት እርስዎ ቀድመው ሊያውቁ ይገባል፤ የርስዎ ማወቅ ህብረሰተብዎን ጥሩ መረጃ እንዲያገኝ፣ ተዘጋጅቶ እንዲጠብቅና እንዲተባበር ይረዳዋል።

ከምንሰጣቸው ስልጠናዎች ለአንዱ እዚህይ መዝገቡ።
**getprepared.nz/ Courses**

ህብረሰተብዎን የበለጠ ለድንገተኛ ግዜ ዝግጁ ለማድረግ ከፈለጉ WREMO በበጎ ፍቃደኝነት ለማገልገል እዚህ ይመዝገቡ።
**getprepared.nz/ Volunteer**

## ሥራዎ ሳይስተጓጎል ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ የነፃ ስልጠና:

የራስዎን የግል ሥራ ወይንም ማህበራዊ ድርጅቶች የሚመሩ ከሆነ በትንሽም ሆነ በብዙ ያለምንም መተጓጎል ሥራዎን መቀጠል ያስፈልጎታል:
ደንበኞችና ሠራተኞች በእርስዎ ላይ ዕምነታቸውን ጥለዋል: እኛ የምንሰጣቸው ስልጠናዎች እርስዎንና ሰራተኞችዎን ከአደጋ በኋላ ሥራዎ ሳይቋረጥ እንዴት መቀጠል እንደሚችልና በውጥረት ግዜ የተሻለ ውሳኔዎችን እንዴት መወሰን እንዳለብዎት ያስተምሮታል: የስልጠናው ተሳታፊዎች ሥራን ያለችግር የማስቀጠል ዕውቀትና በራሳቸው ጥሩ ዕቅድን ማውጣት ተምረው ይሄዳሉ።

ሁለት ሰዓት የሚፈጀውን ስልጠናችንን በመላው የዌሊንግተን አካባቢ እንሰጣለን.

**getprepared.nz/ Businesses**

## የህብረተሰቡ የአደጋ ጊዜ ምላሽ ዕቅድ

እንደርስዎ ያሉ ሰዎች የአደጋ ጊዜ ምላሽ ዕቅድ አስተዋጽዎ ያደርጋሉ።
የራስዎን ህብረተሰብ ሊረዳ የሚችል በቂ ዕውቀት አለዎት፣ ያ የሚረዳ ሊጠቅም የሚችል ነው።
ምን ዓይነት ዕቅድ እንደወጣና እንዴት አስተዋጽዎ እንደሚያደርጉ ወደ **getprepared.org.nz/ ResponsePlan** በመሄድ ይመልከቱ።

**getprepared.nz/ ResponsePlan**

በዚህ አድራሻ ያግኙን:

**wremo@gw.govt.nz**

**04 830 4279**

**facebook.com/WREMOnz**

# በአቅራቢያዎ ያለውን የድንገተኛ አደጋ ግዜ ማዕከል ያለበትን ይወቁ:

## የድንገተኛ አደጋ ግዜ ማዕከሎች ለህብረሰተቡ የመገናኛ ቦታዎች ናቸው:  ቀደም ብሎ የሲቪል መከላከያ ማዕከሎቻችን ተብለዉ ይጠሩ ነበር: በተሻለ መልኩ ዓላማውን እንዲያንፀባርቁ ስማቸውን ቀይረነዋል

ከካባድ የመሬት መናወጥ በኋላ እንደርስዎ ያሉ የህብረተሰቡ አባላት በአቅራቢያው በሚገኘው የድንገተኛ አደጋ ግዜ ማዕከል በመሰባሰብ የማህበረሰብዎን ምላሽ ለማስተባበር ባለው ተገቢ ሞያና አቅርቦት መጠቀም።

በአቅራቢያዎ ያለው የድንገተኛ አደጋ ግዜ ማዕከል የት እንደሆነ ለማወቅ getprepared.nz/Hubs

ማዕከሎቻችን መሠረታዊ የሆኑ የፅህፈት መሳሪያዎችን፣ fm/am ሬድዮ፣ ካርታ፣እብዲሁም ከአደጋ ጊዜ ማእከሎች ጋር እንዲገናኙ የሚረዳ የሲቪል መከላከያ የመገናኛ ሬድዮ በውስጣቸው ይዘዋል ይህም ከአካባቢው ምክር ቤት የአደጋ ግዜ ክንውን ማዕከል ጋር ያገናኛል።
በማዕከሎቹ ተጨማሪ የድንገተኛ አደጋ ግዜ አቅርቦቶች የሉም:



# 2. ዝቅ ማለት፣ መከለል እና መያዝ ይለማመዱ

**ዓለም አቀፍ ባለሞያዎች በመሬት መናወጥ ጊዜ ዝቅ ማለት፣ መከለል እና መያዝ ለጉዳት የመጋለጥን ዕድል እንደሚቀንስ ይመሰክራሉ::**

በመሬት መናወጥ ወቅት በሚፈርስ ህንፃ ከሚጎዱት ይልቅ በቤት ውስጥ ባሉ የቤት ዕቃዎች ወይንም ለጌጥ በተገጠሙ ፍርስራሾች ነው አብዛኛው ጉዳት የሚከሰተው::

## በመሬት መናወጥ ጊዜ :-

**ቤት ውስጥ :-** መሬት መናወጡ እስኪያቆምና ደህንነቱን እስኪያረጋግጡ ድረስ ቤት ውስጥ ይቆዩ:: ከሚወድቁ ነገሮች እራስዎን እየጠበቁ ከቤቱ በጥንቃቄ ይውጡ::

**በረጅም ህንፃ ውስጥ:-** የእሳት አደጋ ማስጠንቀቂያው ደወል ስለጮኸ ብቻ ከህንፃው ለመውጣት አይቸኩሉ ከላይ እንደተጠቀሰው ያድርጉ::

**ውጪ:-** ከህንፃዎች ከዛፎች እና ከኤሌክትሪክ መስመሮች ይራቁ እና መናወጡ እስኪቆም ዝቅ በማለት ከለላ ፈልገው ይያዙ::

በተጨናነቀ የከተማ መንገድ ላይ:- ከህንፃዎች የሚወድቁ ነገሮች ሊመታዎት ስለሚችል በእግረኛ መንገድ ላይ አይቁሙ::

ፈጥነው ወደ ህንጻ ውስጥ ይግቡ ከዚያም ዝቅ በል፣ ተከለልና ያዝ

ዝቅ ማለት፣መከለል እና መያዝ በማይችሉበት ሁኔታ በተቻለዎት ዓቅም እራስዎን ለማዳን ሌላ አማራጮችን ይፈልጉ ጭንቅላትዎን እና አንገትዎን የሚከላከሉበትን መንገድ ይፈልጉ::



# 3. የሱናሚ ዞኖችን ይወቁ

በመሬት መናወጥ ጊዜ የባህር ጠረፍ አካባቢ ከሆኑ እና መናወጡ ለረጅም ግዜ ወይንም ጠንካራ ከሆነ ከአካባቢው በፍጥነት ይራቁ።

የሚደርስዎት ብቸኛው የሱናሚ ማስጠንቀቂያ ራሱ የመሬት መንቀቀጥቀጡ ነው።

ሱናሚ ማለት ለረጅም ሰአት ያለማቋረጥ የሚመጡ ሞገዶች ናቸው። የመጀመሪያ ሞገድ ከባድ ላይሆን ይችላል። በፍጥነት ደህንነቱ ወደተጠበቀ ቦታ የሱናሚ ሰማያዊ መስመሮችን አልፈው ይሂዱ።

ሁሉም ሰው ደህንነቱ ወደተጠበቀ ቦታ መሄድ እንዴት እንደሚችል ከጎረቤቶችዎ ጋር ይነጋገሩ፤ አንዳንድ ሰዎች ከሌላው የበለጠ ዕርዳታ ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

የሚኖሩበት የሚሰሩበት ወይም የሚጫወቱበት ሥፍራ የሱናሚ ዞን ውስጥ መሆን አለመሆኑን እንዲሁም አስፈላጊ ከሆነ ደህንነቱ ወደተጠበቀ ቦታ የት መሄድ እንደሚችሉ ያረጋግጡ።

getprepared.nz/TsunamiZone

ከሱናሚ በኃላ ውሀ ውስጥ ወይንም የባህር ጠረፍ አካባቢ ከመሄድዎ በፊት ሁሉም እስኪረጋጋ ይቆዩ።



10 MIN

የመጀመሪያው ሞገድ በ10 ደቂቃ ውስጥ ሊከሰት ስለሚችል ኦፊሴላዊ ማስጠንቀቂያ ለማስተላለፍ ጊዜ የለም፤ የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያዎችን የምንጠቀመው ከርቀት፤ ለምሳሌ ከደቡብ አሜሪካ አካባቢ ካሉ ቦታዎች ለሚነሱ ሱናሚዎች ነው።

# 4. የቤተሰብ ዕቅድ ያውጡ።

ከከባድ የመሬት መናወጥ በኋላ ስልክ ወይም የተለያዩ ማህበራዊ ድህረገጾች ሊሰሩ ስለማይችሉ አስቀድሞ ሌሎች አማራጭ የሚሆኑ ዕቅዶችን ማውጣት።

## ደህንነቱ የተጠበቀ የመገናኛ ቦታ ለመገናኘት መስማማት:

ቤተሰቡ የሚገናኝበት ደህንነቱ የተጠበቀ የመገናኛ ቦታ መወሰን እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በአደጋ ጊዜ ለቤተሰቡ ማረፊያ ሊሆን የሚችል የቤተ ዘመድ ወይንም ጓደኞች ቤት ማዘጋጀት።

### የልጆችን ደህንነት መጠበቅ።

ትምህርት ቤቶች የልጆችን ደህንነት ለመጠበቅ የራሳቸው ዕቅድ አላቸዉ ።

የልጆችዎን ትምህርት ቤት የአደጋ ጊዜ ዕቅድ ለማወቅ ከፈለጉ www.getprepared.nz/schools በመጎብኘት ማወቅ ይችላላሉ።

ልጆችዎን ከትምህርት ቤት ሊወስዱላችሁ የሚችሉ በትምህርት ቤት አቅራቢያ የሚኖሩ ከሶስት ያላነሱ ቤተዘመዶች ወይንም የጓደኛ አስቀድሞ በማዘጋጀት የስም ዝርዝራቸዉን ለትምህርት ቤታቸው ይስጡ።

ለልጆችዎ በመሬት መናወጥ ጊዜም ሆነ በኋላ ሊከሰቱ የሚችሉትን ነገሮች መንገር እንዲሁም እርስዎ ካልቻሉ ከትምህርት ቤት ማን ሊወስዳቸው እንደሚችል ማሳወቅ።

### የቤትና የንብረት መድን (ዋስትና) መግባት:

ብዙ ሰዎች ዝቅ ባለ ዋስትና ውል ይገኛሉ፣የእርስዎ ቤትና ንብረት በትክክለኛ ዋጋቸው ዋስትና ማግኘታቸውን ዋስትና ከገቡበት ድርጅት ጋር በመነጋገር ማረጋገጥ።



## በቤትና በሥራ ቦታ በቀላሉ ሊያዝ የሚችል ቦርሳ ማዘጋጀት::

የመኖርያ ቤትዎን በአስቸኳይ መልቀቅ ወይንም ከሥራ ቦታዎ ወደቤትዎ ረዘም ያለ መንገድ መራመድ ሊጠበቅብዎ ይችላል:: ላልተወሰኑ ሰዓታት ወይንም ቀናት ሊያቆይዎ የሚችል ምን ዓይነት ቁሳቁስ እንደሚያስፈልጉዎት ያስቡና መሰረታዊ ከሆኑ ዕቃዎች ጋር በቀላሉ ሊያዝ በሚችል ቦርሳ ያስቀምጡ፤ይህንንም በግል በዝቅተኛ ዋጋ ማዘጋጀት ይቻላል::

ለበለጠ መረጃ **getprepared.nz/GrabBag** ይጎብኙ:

## መገልገያዎች:

በቤትዎ ውስጥ የተገጠሙ የመገልገያ ምንጮች አደገኛ ስለሚሆኑ በቤትዎ መቆየት ሊያግድዎት ይችላል::

የጋዝ ተጠቃሚ ከሆኑ የጋዝ፣ የውሀ፣ እንዲሁም የኤሌክትሪክ ቆጣሪዎች ያሉበትን ቦታ በማግኘት እንዴት መዝጋት እንደሚችሉ ይወቁ፤ በቀላሉ ለማግኘት እንዲረዳዎም ግልጽ የሆነ ምልክት ያድርጉ::



# 5. ቤትዎን ደህንነቱ የተጠበቀ ያድርጉ

በጡብ የተሰሩ የጭስ ማውጫዎችን ደህንነት ማረጋገጥ።
የጭስ ማውጫዎን የማይጠቀሙበት ከሆነ ያስወግዱት።

የውሀ ማጠራቀሚያ ታንኮች ከዳን በደንብ መዘጋቱን ያረጋግጡ።

ማንኛውም በጣራው ውስጥ የበሰበሰ ወይም የጎደለ ቋሚ ወይም ማገር ካለ ይተኩ።

ቤትዎን ደህንነቱ የተጠበቀ ማድረግ በመሬት መንቀጥቀጥ ጊዜ የሚከሰቱ ጉዳቶችን ይቀንሳል፤ ቤትዎ በትንሹ ቢጎዳም ሊኖሩበት የሚያስችል ይሆናል።


የቤትዎን መሠረት ግድግዳና ጣራ እንዲሁም በቤት ውስጥ የሚገኙ ዕቃዎች ደህንነት ያረጋግጡ። .

እርዳታ ካስፈለገዎት የቤትዎን ደህንነት በሙያተኛ ያስመርምሩ።

ቤትዎ ለመሬት መናወጥ ክስተት ደህንነቱ ስለመረጋገጡ ይወቁ ። getprepared.nz/SafeHomes

**ተከራይተው ከሆነ የሚኖሩት:**

ከመሬት መናወጥ በኋላ ቤትዎ ለመኖርያነት ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጡ የአከራይ ድርሻ ነው።ይህን መመርያ በመጠቀም የቤትዎን ደህንነት እንዴት መጠበቅ እንዳለበት ከአከራዩ ጋር ይነጋገሩ።



ከባድ ወይም ረጅም የቤት ዕቃዎች አስተማማኝ ሆነውይጠበቁ።

ላልተጠናከሩ የቤቱ ግድግዳዎች ተጨማሪ ድጋፍ ያድርጉ።

የሙቅ ውሀ መያዢያ ዕቃና የእንጨት ማገዶ አስቀምጥ።

# 6. ውሀ ያጠራቅሙ


## ከትልቅ የመሬት መናወጥ በኃላ የውሀ አቅርቦት ስለማይኖር ለአደጋ ጊዜ የሚሆን ውሀ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። በብዛት ማዛጋጀት ከተቻለ የተሻለ ነው፤ ለመላ ቤተሰቡ ለአንድ ሳምንት እንኳን የሚበቃ ውሀ ማዘጋጀት አለብዎ።


በዚህ ሳምንት መጨረሻ 200 ሊትር ወይንም ከተቻለ ከዛ የበለጠ የውሀ ማጠራቀሚያ ታንክ ይግዙ: ይሄም ለአደጋ ጊዜ የሚሆን በቂ ውሀ እንዲያጠራቅሙ ይረዳዎታል። ዋጋው ተመጣጣኝና በቀላሉ የሚገጣጠሙ ናቸው ባስተማማኝ ይግጠሙትና የውሀ ማጠራቀሚያውን በንፁ ውሀ ይሙሉት።

getprepared.nz/Water

የውሀ ማጠራቀሚያ ታንክ መግዛት ካልቻሉ ሌላ አማራጮችን ይጠቀሙ። ትልልቅ የውሀ መያዣ ፕላስቲኮችን ለውሀ ማጠራቀሚያ ይጠቀሙ የወተት መያዣ ኮዳዎችን ለውሀ ማጠራቀሚያ መጠቀም አይመከርም: በኮዳው ውስጥ የሚቀረው የወተት ጠብታ ውሀውን ሊመርዘው ይችላል።

የውሀ ማጠራቀሚያዎቹን በደንብ ከሞሉት በኃላ መዘጋቱን ያረጋግጡና ቀዝቃዛና ጨለም ያለ ቦታ ማስቀመጥ እንዳለብዎ አይዘንጉ። በየ12 ወሩ ውሀውን መቀየር ይኖርብዎታል።



# 7. ከጎረቤቶችዎ ጋር ይገናኙ

ብዙ ሰዎች ከአደጋ የሚተርፉት አጠገባቸው ባሉት ሰዎች ነው፤ ጎረቤቶች የመጀመሪያ የአደጋ ጊዜ ረዳቶች ናቸው::

በዚህ ሳምንት መጨረሻ በቤትህ መንገድ ከሚገኙ ሰዋች ጋር ተዋወቅ በማንኛውም አስቸኳይ ግዜ ሁሉም ሰው ደህንነቱ የተጠበቀና ተንከባካቢ ያለው መሆኑን፧

- ከሁሉ በላይ ደግሞ የተለየ ዕርዳታ የሚሹ እንዳሉ አረጋግጥ::
- እርስ በርስ ለመረዳዳት ቁሳቁስና ችሎታን ተከፋፈሉ።
- እርስ በርስ መተጋገዛችሁን ቀጥሉ:

getprepared.nz/Neighbours

በበለጠም በዓመቱ ውስጥ ያሉትን እያንዳንዷን ቀን ወዳጅነቱ የተጠበቀና ጠንካራ ማህበርሰብ ለመገንባት ትረዳለህ::

የሚከብደው የመጀመሪያውን እርምጃ መውሰድ ነው፤ ነገር ግን በትንሽ ፈገግታና እራስን በማስተዋወቅ መጀመር ከዚያም ለአደጋ ግዜ እንዲጠቅማችሁ ስልክ ቁጥር እንድትቀያየሩ ጥቂቶችን መጠየቅ ቀለል ያለ የመግባቢያ መንገድ ነው::

በሚኖሩበት አካባቢ የአካባቢ መረዳጃ ቡድን መጀመር ወይንም በአቅራቢያው ያለ Timebank መቀላቀል::

በተወሰኑ ሳምንታት ልዩነት ከጎረቤቶች ጋር መገናኛ የሚሆኑ ፕሮግራሞች ማዘጋጀት ::



# 8. በቤት ውስጥ ካምፕ ለማድረግ ይሞክሩ

ቤትዎ የዕለት ተዕለት ተራ ዕቃ መስለው በተቀመጡ ግን ለድንገተኛ ጊዜ ከፍተኛ ጥቅም ባላቸው ነገሮች የተሞላ ነው።

አልጋዎ ላይ ያለው የብርድ ልብስ ቁምሳጥን ውስጥ ያስቀመጡት ልብስ በማድቤት ያሉ ቁሳቁስ በሙሉ ለድንገተኛ ጊዜ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

- ልጆች፣ ህጻናት እና የቤት እንስሳት ካለዎት በቂ አቅርቦት ያዘጋጁ።
- የመድሀኒቶችዎ ዝርዝር ይኑርዎት በቂ አቅርቦትም እንዳለዎት ያረጋግጡ።

በድንገተኛ አደጋ ጊዜ እራስዎንና እና ቤተሰብዎን በመርዳትዎ የአደጋ ጊዜ ሰራተኞች ያላቸውን ውስን አቅርቦታቸውን በጣም ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች እንዲጠቀሙ ይረዷቸዋል።




1 2 3 4 5 6 7 ተዘጋጅተናል! ✓ እኛ ለአንድ ሳምንት የሚበቃ የአደጋ ጊዜ አቅርቦት አለን።



## getprepared.nz ላይ ሆነው:

1. የአካባቢውን የአደጋ ጊዜ ምላሽ ዕቅድ ለማወቅ ከላይ የተጠቀሰውን የአካባቢውን ማዕከል የአገናኝ አድራሻ ይከተሉ።
2. የአካባቢውን የአደጋ ጊዜ ምላሽ ዕቅድ ለማወቅ ከላይ የተጠቀሰውን የአካባቢውን ማዕከል የአገናኝ አድራሻ ይከተሉ።
3. በአደጋ ጊዜ የሚታመን መልእዕት ለማግኘት www.wremo.nz

# ከመሬት መናወጥ በኋላ :

## በሱናሚ አደጋ ውስጥ ነው ያሉት?

- ደህንነቱ ወደተጠበቀ ደረቅ ወይንም ከፍ ወዳለ ቦታ በእግር ወይንም በሳይክል ይሂዱ፤ መኪና እንዳይነዱ።
- የሱናሚ ሰማያዊ ቀስቶችና የመልቀቂያ መሄጃ አቅጣጫዎችን ተከትለው በአቅራቢያዎ ወዳለ ደህና አካባቢ ወይም ከሱናሚ ሰማያዊ መስመሮች በላይ ይከተሉ። ከኋላዎ ለሚመጡ ለሌሎች ቦታእንዲያገኙ ጉዞዎን ይቀጥሉ።

## ከሌሎች ጋር ይገናኙ :

- ወደቤትዎ ለመሄድ ከመሞከርዎ በፊት ከቤተሰብዎ ጋር ተስማምተው በመረጡት ደህንነቱ በተጠበቀቦታ ይገኙ።
- ከተቻለዎት በማህበራዊ ድረገጾች ወይም በድምጽ መልዕክት ለሌች ደህና መሆንዎን ይግለጹ። የኔት ወርክ መጨናነቅን ለመቀነስ ከመደወል ይልቅ የፅሁፍ መልእክትን ይጠቀሙ።

## ልጆችን ካሉበት ይሰብስቡ ;

- ሁሉም ሰው የአደጋ ጊዜ ዕቅድ ምን እንደሆነ እንደሚያውቁ ያረጋግጡ፤ ልጆች ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ሳሉ ወደትምህርት ቤት በመሄድ እራስዎን አደጋ ላይ አይጣሉ። ሁሉም ነገር ከተረጋጋ በኋላ ልጆችዎን ከያሉበት ይሰብስቡ።

## ቤትዎን ደህንነቱ የተጠበቀ ያድርጉት;

- የሚተነፍስ ጋዝ ከሰሙ ወይንም ከሸተተዎት ፍንዳታን ለመከላከል ይዝጉት።
- ኤሌክትሪክ ከተቋረጠ ወይንም ቦታውን መልቀቅ ካለብዎት ኤሌክትሪኩን አጥፍተው ይውጡ ምክንያቱም ሊያዩአቸው የማይችሉ የተጎዱ ገመዶች ሊኖሩ ስለሚችሉ ።
- የውሀ ቧንቧዎች ላይ ጉዳት ደርሷል ብለው ካሰቡ ውሀውን ከዋናው መዝጋት አይዘንጉ፤ የውሀ ፍሳሽ ቤትዎ ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል።

## ውሀና የንፅህና አጠባበቅ:

- ያልተጣራን ውሀ ከመጠቀምዎ በፊት ለአንድ ደቂቃ ያፍሉት ወይንም ግማሽ የሻይ ማንኪያ ሽቶ ያልተዋሃደበት በረኪና በ10 ሊትር ውሀ ይጨምሩ። ከመጠጣትዎ በፊት ለ30 ደቂቃ ያቆዩት።
- የመፀዳጃ ቤት ውሀ አይጠቀሙ; ጉድጓድ ቆፍረው ይጠቀሙ; ንፅህናዎን ይጠብቁ ።

## የጌረቤቶችዎን ደህንነት ያረጋግጡ:-

- እንቅስቃሴው ውሱን የሆነ ብቻውን የሚኖር ሰው ተጨማሪ ዕርዳታ ሊያስፈልገው ስለሚችል አትኩሮት ይስጡ።
- ያለዎትን አቅርቦትና ዕውቀት በማካፈል እርስ በርስ ተረዳዱ ።

## አቅራቢያዎ ያለው የአደጋ ጊዜ ማዕከል ይሂዱ።

- እርዳታ ካስፈለገዎት ።
- በዕውቀትም ሆነ በቁሳቁስ ድጋፍ መስጠት የሚችሉ ከሆነ።
- በአካባቢዎ ስለ ሆው ነገር መረጃ ለማግኘት ወይም ለማካፈል ከፈለጉ :
- የህብረሰተብዎን ምላሽ ባአካባቢዎ ለማስተባበር እና ለክልሉ ምክር ቤት የድንገተኛ ግዜ ማስተባበሪያ ማዕከል መረጃ ለማካፈል

ከፈለጉ www.wremo.nz ይጎብኙ። እንዲሁም ስለ አስቸኳይ ግዜ መረጃ ራድዮ ያዳምጡ።

# ዝግጁ ነን!

የቤተሰብ መገናኛ ቦታ:

ልጆቻችንን ከትምህርት ቤት መውሰድ የሚችሉ ሰዎች ዝርዝር:

የህብረተሰባችን ማዕከል ነው :

የጎረቤቶቻችን ስልክ ቁጥሮች:-

መገልገያዎቻችን የሚገኙበት ቦት:

ውሀ:-

ኤሌክትሪክ:-

ጋዝ:-

ለአደጋ ጊዜ ዝግጅት መረጃ www.getprepared.nz ይጎብኙ።

በማድቤት የዕቃ መደርደሪያ ውስጥ ይለጥፉት: